# ለ2022 የSummer Program Fund የእቅድ ማቅረቢያ ፕሮፖዛል (RFP)

*የገንዘብ ድጋፉ በWashington ግዛት፣ በሱፐር ኢንቴንደንት ኦፍ ፐብሊክ ኢንስትራክሽን (OSPI) ቀርቧል*
*በSchool's Out Washington (SOWA) ረቅቋል እንዲሁም አገልግሎት ላይ ውሏል*

**ማመልከቻዎች የሚያበቁት በሰኞ፣ ዲሴምበር 6፣2021 በ11:59 PM ይሆናል።**

## መግቢያ

የ Office of the Superintendent of Public Instruction (OSPI) የ2022ቱን የSummer Program Fund ለማርቀቅ እና አገልግሎት ላይ ለማዋል ከSchool's Out Washington (SOWA) ጋር አጋር ሆኗል። እነዚህ የገንዘብ ድጋፎች የአሜሪካን ሬስኪዩ ፕላን/ ESSER (Elementary and Secondary School Emergency Relief) ግብዓቶችን የሚጠቀመው የOSPI የሁለት ዓመት የበጋ መርሃ-ግብር ኢንቨስትመንት አካል ናቸው። የበጋ መርሃ-ግብር የገንዘብ ድጋፍ ዋነኛው ዓላማ[1] ማህበራዊ ግንኙነቶችን፣ አካላዊ እና ከቤት ውጪ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን የሚያካትቱት የ2021 እና 2022 የበጋ ትምህርት ፕሮግራሞች ላይ እንዲሳተፉ ከትምህርት የፍትህ ስርዓት ለራቁ ለWashington ታዳጊዎች እድሎችን ማስፋት ነው።

ከ2020 የፀደይ ወቅት ጀምሮ፣ የኮቪድ-19 በሽታ የቤተሰቦችን፣ ትምህርት ቤቶችን እንዲሁም የወጣት ማሰልጠኛ ድርጅቶችን የተማሪዎችን ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ አእምሯዊ ጤና እና ትምህርት ነክ ፍላጎቶችን ሙሉ በሙሉ እና በስኬታማነት ለማሟላት ያላቸውን አቅም አደጋ ላይ ጥሏል። ታዳጊዎች በኮምፒዩተር በኩል በሚሰጡ ትምህርቶች መገደብ ምክንያት ተገልለዋል እንዲሁም ቤተሰቦች የልጅ እንክብካቤን በተመለከተ ትግል ውስጥ ገብተዋል። ከትምህርት የፍትህ ስርዓት ውጪ ላሉ ታዳጊዎች፣ የተገደቡ የፕሮግራሞችና የአገልግሎቶች ግንኙነቶች ነባር ፍትህ አልባ ሂደቶችን አባብሰዋል።

ተግዳሮቶቹ ቢኖሩም እንኳን፣ የወጣት ማሰልጠኛ ድርጅቶች በጥልቀት ለሚቀርቧቸው ለወጣቶቹ እና ለቤተሰቦቻቸው ምላሽ እንዲሰጡ በሚያስችል መልኩ አገልግሎቶቻቸውን አሻሽለዋል። የኮቪድ-19 ጉዳት እየቀለለ እየሄደ ባለበት ሁኔታ እነዚህ ድርጅቶች በመዘጋት እና በመገለል አማካኝነት በታዳጊዎች መካከል የጠፉትን ማህበራዊ ግንኙነቶች የሚያሻሽሉ፣ ለአካላዊ እና ከቤት ውጪ ለሆኑ እንቅስቃሴዎች እድል የሚሰጡ እንዲሁም Washington ከበሽታው አገግማ ስትነሳ የታዳጊዎችን ደህንነት የሚያጠናክሩ የበጋ 2022 መርሃ-ግብሮችን በማህበረሰቦቻቸው ውስጥ ለመስጠት በትክክለኛ ቦታን ይዘዋል።

## RFP አጠቃላይ እይታ

የ2022 የSummer Program Fund በ2021 የSummer Program Fund በተገኙ ትምህርቶች ላይ ተመስርቶ ይገነባል። በጥብቅ በተጣሉ ገደቦች ውስጥ በመስራት $1 ሚሊዮን በኦገስት፣2021 ካመለከቱት ከ277ቱ ድርጅቶች ለተወጣጡ

---

[1] ለ2022 የበጋ መርሃ-ግብር የገንዘብ እርዳታ ዓላማ፣ ከትምህርት ፍትህ በጣም ርቀው የሚገኙ ወጣቶች የሚከተሉትን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የወጣቶች ብዛት በማካተት ይገለፃሉ፡ በድህነት ውስጥ ያሉ ወጣቶች፣ BIPOC (ጥቁር፣ ተወላጆች እና የቀለም ሰዎች) ወጣቶች፣ ስደተኛ ወጣቶች፣ ስደተኛ እና/ወይም የተሰደዱ ወጣቶች፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች፣ የጎዳና ተዳዳሪነትን እያሳለፉ ያሉ ወጣቶች፣ በአሳዳጊ ስር ያሉ ወጣቶች፣ LGBTQ ወጣቶች በወንጀል ፍትህ ሥርዓት ውስጥ የተሳተፉ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኛ ወጣቶች።

ለ62 ስኬታማ አመልካቾች ተከፋፍሏል። የገንዘብ ድጋፍ የነበራቸው ፕሮግራሞች ከ$5,000 እስከ $25,000 ተቀብለዋል።

ለበጋ 2022፣ በአማካይ $4.5 ሚሊዮን ከ$10,000- $50,000 ባለው ገደብ ተመቻችቶ ለመርሃ-ግብር የገንዘብ ድጋፍ ይቀርባል። ሂደቱ እና የጊዜ ሰሌዳው ተለቅ ያሉ ሽልማቶችን እና በዛ ያለ ቁጥር ያላቸው የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻዎችን ያስተናግዳል። የ2022 የበጋ ገንዘብ ድጋፍ መርሃ-ግብር የመጀመሪያውን የበጋ መርሃ-ግብር እቅድ እና ማመልከቻ ለማስገባት ረዘም ያለ የጊዜ መስኮትን ያቀርባል።

SOWA የተለያዩ ድርጅቶችን ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የበጋ ፕሮግራሞች እንዲያቀርቡ እና ዝቅተኛ አገልግሎት ለሚያገኙ ማህበረሰቦች ዕድልን እንዲያስፋፉ የሚያበረታ ፍትሀዊ እና በቀላሉ ሊገኝ የሚችል ሂደትን ያካሂዳል።

**ብቁ አመልካቾች**

አንድን ማመልከቻ ለማስገባት ብቁ ለመሆን ድርጅቶች የበጋ ፕሮግራሞቻቸው ማህበራዊ ግንኙነቶች እንዲሁም አካላዊ እና ከቤት ውጪ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን እንደሚያካትቱ ሊያረጋግጡ ይገባል። እባክዎትን**ብቁ የሆነን መርሃ-ግብር**(ከታች) ለተጨማሪ መረጃ ይመልከቱ።

ትርፍ የለሽ ማህበረሰብ መር ድርጅቶች (Community Based Organizations CBOዎች)፣ የሀይማኖት ተቋማትን ጨምሮ፣ ለገንዘብ ድጋፍ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። ትናንሽ ንግዶች እና የህዝብ ተቋማትም ለማመልከት ብቁ ናቸው።

ለሀይማኖት ተቋማት የሚደረጉ የገንዘብ ድጋፎች የሀይማኖት መርሃ-ግብሮችን ወይም ቁሳቁሶችን አይደግፉም፣ እንዲሁም (እንደ ጸሎቶች እና ሀይማኖታዊ ዓላማ ያላቸው ትምህርቶች በመሳሰሉ) በሀይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ ለወጣት ተሳታፊዎች እንደቅድመ ሁኔታ አይቀመጥም።

እንደአነስተኛ ንግዶች ለማመልከት የሚያስቡ አመልካቾች የአነስተኛ ንግዶችን ምንነት ማሟላት ይገባቸዋል በRCW (Revised Code of Washington) 19.85.020፣ በግልጽ፡ , *"ትንሽ ንግድ" ማለት ማንኛውም የንግድ አካል ሆኖ፣ የግል ባለንብረትነት ያለው፣ ኮርፖሬሽን፣ አጋርነት አልያም ሌላ ህጋዊ አካልን የሚያካትት፣ ከሌሎች ንግዶች ሁሉ ነጻ በሆነ መልኩ የተያዘ እና የሚመራ እንዲሁም ሀምሳ ወይም ከዛ በታች ሰራተኞች ያሉት ነው"*

የመናፈሻ መስሪያ ቤቶች እና የትምህርት ቤት ክልሎች ብቁ አይደሉም፤ OSPI ለእነዚህ አካላት የተመደቡ ሌሎች የገንዘብ ድጋፎች አሉት።

የበጋ የገንዘብ ድጋፎች በWashington ግዛት ያሉ ታዳጊዎችን ለሚያገለግሉ ድርጅቶች ብቻ ይመቻቻሉ። የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራሞች ከWashington State Department of Healthፕሮቶኮልሰ ጋር መስማማት አለባቸው።

ብቁ ለመሆን አመልካቾች እድሜያቸው ለትምህርት ለደረሰ ከ4-21 ዓመት ለሚሆናቸው ከኬጂ-12 ባሉ ትምህርትቤቶች ውስጥ ለገቡ አልያም ለሚገለገሉ ታዳጊዎች ያላቸውን የበጋ ፕሮግራማቸውን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ታዳጊዎች ከኬጂ-12 ባሉ የትምህርት ቤት ተቋማት ውስጥ በጋን የሚዳስሱ አገልግሎቶች መቀበል አይጠበቅባቸውም፤ ነገር ግን ከኬጂ-12 ባሉ ትምህርት ቤቶች ውስጥ መግባት አልያም አገልግሎቶችን በትምህርት ዓመቱ በሆነ ሰዓት ላይ ማግኘት ይኖርባቸዋል። የቤት ውስጥ የትምህርት ክትትል የሚያደርጉ ታዳጊዎችም በበጋ ፕሮግራሞች ላይ መገልገል ይችላሉ።

ከእያንዳንዱ ድርጅት አንድ ማመልከቻ ብቻ ተቀባይነት ይኖረዋል። ብቸኛው ቅሪት ለሌላ ብቁ ድርጅት እንደ ገንዘብ ድጋፍ ሰጪ[2] ለሚያገለግል አመልካች ነው። በእንደዚህ አይነት ጉዳዮች ወቅት እያንዳንዱ ማመልከቻ ማስገባት ይችላል።

ብዙ የገንዘብ አጋሮች ላሏቸው ድርጅቶች እንዳንዱ አጋር የየራሱ 501(c)(3) ትርፍ አልባ የግብር ሁኔታ እና የየራሱ የግብር መለያ ቁጥር ያለው ከሆነ በነፍስ ወከፍ ማመልከት ይችላል።

**ብቁ መርሃ-ግብር ማድረግ:**
በግዛቱ ህግ ላይ በተቀመጠው መርህ መሰረት በመተግበር፣ OSPI እነዚህን የገንዘብ ድጋፎች በታዳጊዎች መካከል ያሉትን **ማህበራዊ ግንኙነቶች** ለማጠንከር እንዲሁም ታዳጊዎችን በ**አካላዊ[3] እና ከቤት ውጪ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች** ላይ ለማሳተፍ ሊጠቀምባቸው ራሱን ሰጥቷል።

በመግለጫው ላይ አመልካቾች ፕሮግራሞቻቸው የሚያካትቷቸውን ማህበራዊ ግንኙነቶችን፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን እና ከቤት ውጪ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን እንዲገልጹ እንዲሁም የበጋ ፕሮግራማቸው ለመተግበር ለምን ቀላል እንደሆነ እና እንዴት ለሚያገለግሏቸው ታዳጊዎች ምላሽ የ ሚሰጥ እንደሆነ እንዲወያዩ ይደረጋል።

የ2022 የበጋ መርሃ-ግብር በብዙ ቀናት እና/አልያም ብዙ ሳምንታት እንዲሰጥ ይደረጋል። በታዳጊዎች መካከል ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት ማጠንከር አስፈላጊ ነገር ስለሆነ የ1፡1 (አንድ አዋቂ ለአንድ ታዳጊ) ላይ ትኩረት የሚያደርጉ እንቅስቃሴዎች ያሏቸው የበጋ ፕሮግራሞች የብቁነት መስፈርቱን አያሟሉም። ፕሮግራሞቹ በአካል ተገኝተው የሚደረጉ አልያም በአብዛኛው በአካል ተገኝተው የሚደረጉ መሆን አለባቸው። ጥቂት ቅይጥ ክፍሎች ወይም ኮምፒዩተርን መሰረት ያደረጉ ተሳትፎዎች ይፈቀዳሉ።

**የጊዜ ሰሌዳ፡**
በግዛቱ ዙሪያ ካሉ ከታዳጊ ማሰልጠኛ ተሳታፊ አካላት የመነጩ ተሳትፎ እና መመሪያ የSummer Program Fundን ለማመቻቸት ቁልፍ ሚና ተጫውቷል። የ2021ዱ የSummer Program Fund RFP ከመሰጠቱ በፊት፣ SOWA በስልት ማርቀቅ እና መተግበር ጉዳዮች ላይ የተሳታፊ አካላትን ግብዓቶች ይፈልግ ነበር። የ2022ቱን የSummer Program Fund ሂደት መረጃ ለመስጠት፣ የ2021ዱ የገንዘብ ድጋፍ እንደተጠናቀቀ SOWA ድጋፍ ከተቀበሉና ካልተቀበሉ ድርጅቶች ግብረመልስ ሰብስቦ ነበር። ከ2021ዱ የSummer Program Fund የአቻ ታዛቢዎች የተገኙ አስተያየቶች እንዲሁም በኦክቶበር የመጀመሪያዎቹ ጊዜያት የነበሩ ተጨማሪ ስብሰባዎች፣ SOWA በቀሰማቸው ትምህርቶች ላይ እንዲተገብር አቅም እንዲኖረው እጅግ ጠቃሚ ነበሩ እንዲሁም የበጋ መርሃ-ግብር ገንዘብ ድጋፉን የፕሮግራሙ የገንዘብ ድጋፍ አካሄድ በማሻሻል ላይ ይገኛሉ።

ለ2022ቱ የSummer Program Fund የኦንላይን ማመልከቻ ሀሙስ፣ኖቬምበር 4፣2021 ይከፈታል፤ የማመልከቻዎቹ ማብቂያ ቀን ሰኞ፣ ዲሴምበር6፣ 2021 በ11፡59 PM ይሆናል። በማመልከቻቸው ላይ ስኬታማ የሆኑ ፕሮግራሞች የገንዘብ ድጋፍ ማስታወቂያ በፌብሩዋሪ 2022 አጋማሽ መቀበል ይኖርባቸዋል። ስኬታማ ለሆኑ አመልካቾች የገንዘብ ድጋፎቹ በሜይ አጋማሽ 2022 ይለቀቁላቸዋል። ለስኬታማ አመልካቾች የመስሪያ ቦታ በማርች 2022 ይሰጣቸዋል። (ይበልጥ ዝርዝር የጊዜ ሰሌዳ ከታች ተካትቷል።)

---

[2] የገንዘብ እርዳታ አቅራቢ በIRS (Internal Revenue Service) 501(c) ከቀረጥ ነፃ የሆነ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን (3) ሌላ የ501 (c) (3) ከቀረጥ ነፃ ሁኔታ የሌለው (ወይም ገና ለሌለው) ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅትን ወክሎ ገንዘብ ለመቀበል የተስማማ ነው። የገንዘብ እርዳታ አቅራቢ ያላቸው አመልካቾች የገንዘብ እርዳታ ስምምነት ቅጿ እንዲያቀርቡ ይገደዳሉ።
[3] አካላዊ እንቅስቃሴዎች ለወጣቶች ሰውነታቸውን በንቃት የሚያንቀሳቅሱበት እና ጉልበታቸውን የሚያጠፉበት አጋጣሚዎች ተብለው ይገለፃሉ።

**ሂደት፡**
የ2022 የSummer Program Fund ማመልከቻዎች ኦንላይን እና በእንግሊዘኛ ማስረከብ ይኖርብዎታል። ነገር ግን RFPው ራሱ ወደ አማርኛ፣ አረብኛ፣ ማንዳሪን ቻይንኛ፣ ኮሪያኛ፣ ማርሻልኛ፣ ሩሲያኛ፣ ሳሞዋኛ፣ ሶማሊኛ፣ ስፔንኛ፣ ታጋሎግኛ፣ ቶንጋንኛ፣ ዩክሬንኛ እና ቪየትናምኛ ይተረጎማል። የተተረጎሙ RFPዎችን ለማግኘት የሚያስፈልግዎት መረጃ በ SOWA የ2022 የSummer Program Fund ድህረ-ገጽ ይገኛል።

የኦንላይን ሂደቱ አመልካቾች ቅጻቸውን ከማስረከባቸው በፊት ብቁነታቸውን እንዲያረጋግጡ ይጠይቃል። ኦንላይን ማመልከቻው ስለአመልካቾቹ የበጋ ፕሮግራሞች እና ድርጅቶች አጠር ያሉ ዝርዝር መረጃዎችን እና መግለጫዎችን ይጠይቃል። አንዳንዱ መረጃ በElevateWashington.org ይካተታል።.

ለገንዘብ ድጋፍ መጠይቆቻቸው ግልጽ የሆኑ የአመልካቾች ምላሾች ወራጅ አማራጮችን እና ሶስቱን የ2022 የSummer Program Fund የትኩረት አካባቢዎችን የሚዳስሱ አጫጭር ትረካዎችን የሚያካትቱ ይሆናል፡

1. ፕሮግራሙ ከትምህርት ፍትሃዊነት እጅግ የራቁ ታዳጊዎችን ያገናኛል።
2. ሰራተኞች፣በጎ ፈቃደኞች አመራር እና የአመልካቹ ድርጅት ቦርድ አባላት ቅድሚያ የሚገለገሉትን ህዝቦች ያንጸባርቃሉ።
3. ፕሮግራሙ ማህበራዊ ግንኙነቶችን፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲሁም ከቤት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎችን ለታዳጊዎች ይገልጻል እንዲሁም ይደግፋል**በተጨማሪም** የፕሮግራሙ ትግበራ እቅድ እነዚህ የፕሮግራሙ ቅድመ ሁኔታዎች እንደሚሟሉ እና ለተገልጋዮች ታዳጊዎች መሰረታዊ ፍላጎቶች እንዲሁም መስህቦች ምላሽ እንደሚሰጡ ያረጋግጣል።

አመልካቾች ድርጅታቸው ቅርብ ጊዜ በተጠናቀቀው የበጀት አመት ስራ ላይ ያዋለውን አጠቃላይ ወጪ በአሀዝ እንዲያቀርብ ይጠየቃሉ።

አመልካቾች ከ$10,000 እስከ $50,000 ያለ የድጋፍ መጠን ይጠይቃሉ።

ምንም አይነት የበጀት ቅጽ አያስፈልግም

## ቴክኒካዊ እገዛ

ስለ RFP እና ማመልከቻው ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚኖሩ የመረጃ ክፍለ ጊዜዎች በZoom ዌቢናር ረቡዕ ኖቬምበር 10፣2021 ከ1:00ፒኤም-2:30 ፒኤም ፒኤስቲ እንዲ ሁም በማክሰኞ፣ ኖቬምበር 16፣2021 ከ9:00 ኤ ኤም- 10:30 ኤኤም ፒኤስ ቲ ይሆናሉ። ሊያመለክቱ የሚችሉ አመልካቾች እንዲሳተፉ ይበረታታሉ። እባክዎ የ SOWAን የ2022 የSummer Program Fund ድህረ-ገጽ ለተጨማሪ መረጃ ይጎብኙ። ለመመዝገብ፣ ከታች ካሉት ቀናት አንዱን ይጫኑ፡

ኖቬምበር 10፣2021፣ 1:00 ፒኤም-2:30ፒኤም
ኖቬምበር 16፣2021፣ 9:00ኤኤም-10:30ኤኤም

ስለ RFP እና ማመልከቻው በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች በየ2022 የSummer Program Fund ድህረ-ገጽ ይገኛሉ። በመረጃ ክፍለጊዜዎች ወቅት አልያም በኢ-ሜይል የተቀበልናቸው ጥያቄዎች ሁሉ እንዲሁም ከ2021 የበጋ ገንዘብ ድጋፍ ሂደቶች የመጡ ተተግባሪ FAQዎች ይለጠፋሉ። ለ FAQ ማሻሻያዎች ለተተነበዩ ቀናት እባክዎ የጊዜ ሰሌዳውን ይመልከቱ።

SOWA ድርጅቶች ለ2022ቱ የበጋ ገንዘብ ድጋፍ ብቁነታቸውን እንዲያውቁ እንዲሁም ማመልከቻቸውን እንዲጨርሱ ለአማራጭ ቴክኒካዊ እገዛ(TA) አቅራቦትን ያመቻቻል። በ SOWA በቀጥታ ከሚሰጠው TA (Technical Assistance) በተጨማሪ በስሞል ቢዝነስ ሬዚሊየንሲ ኔትወርክ በኩል የሚመቻች እርዳታም ይኖራል። የ Washington State Department of Commerce ባህላዊ ጠቀሜታ ያላቸውን እርዳታዎች ለትናንሽ ንግዶች እና ትርፍ አልባ ድርጅቶች ለማቅረብ ከነዚህ የተለያዩ ተአማኒነት ያላቸው ድርጅቶች መረብ ጋር በአጋርነት ይሰራል። ቴክኒካዊ እገዛን የማግኘት ፍላጎት ያላቸው አመልካቾች የ[የ2022 የSummer Program Fund ድህረ-ገጽ ]ን ማማከር አለባቸው።

# የፕሮፖዛል እርማት ሂደት

በግዛቱ ዙሪያ ካሉ አጋሮች ጋር በመተባበር SOWA በአማካይ 60 የፕሮፖዛል አራሚዎችን በጠንካራ ክልላዊ እና በBIPOC (Black, Indigenous, People of Color) (ጥቁር፣ ሀገር በቀል፣ የቀለም ሰዎች) ውክልና ላይ ትኩረት ባደረገ መልኩ ለማግኘት በመስፋት ላይ ያለ ተደራሽነትን እተከተለ ነው። ሊመረጡ የሚችሉ አራሚዎች መኖሪያቸው በWashington የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ ነው። ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ህዝቦች ለመወከል መስፈርት ከማሟላት እና ማመልከቻዎችን ከማረም ልምድ በተጨማሪ፣ አራሚዎች ክልሉን ያማከለ እውቀት እና ጥልቅ የሆነ የWashington ታዳጊዎች ማሰልጠኛ አካባቢያዊ መረዳቶች ሊኖራቸው ይገባል።

ሁሉም አራሚዎች የጥቅም ግጭቶችን በግልጽ እንዲያወጡ ይጠየቃሉ። የክለሳ የቡድን ምደባዎች ማንም አራሚ እንደሰራተኛ፣ የቦርድ አባል አልያም አማካሪ ከተቀጠረበት ድርጅት/መርሃ-ግብር የሚመጡ መጠይቆችን እንዲያነብ እንደማይመደብ ያረጋግጣሉ። SOWA የፀረ-መድሎ ስልጠናን ይጠይቃል እንዲሁም የማመልከቻ ጥያቄዎቹን እና የውጤት አሰጣጡን እንደአስገዳጅ የአራሚ ስልጠና አካል ይወያይበታል።

አራሚዎች ከራሳቸው ክልል የሚመጡ መጠይቆችን ይመለከታሉ። እንደአራሚ የሚያገለግሉ በግዛቱ ዙሪያ ያሉ አጋሮች በሁሉም ክልሎች ባሉ ቡድኖች ዙሪያ ይበተናሉ።

አራሚዎች በግላቸው በአማካይ ለ20 ማመልከቻዎች ውጤት ይሰጣሉ። የግል ነጥብ ተይዞ ካለቀ በኋላ አንድ አይነት መጠይቆችን ነጥብ ከሰጧቸው አራሚዎች የተወጣጡ ትናንሽ ቡድኖች የውጤት መስጫ ሳጥናቸው ላይ ይነጋገራሉ ከዚያም ለእያንዳንዱ ማመልከቻ ሁሉንም የሚያስማማ ውጤት ይወስናሉ። የአራሚ ቡድኖች በመሪ አራሚዎች ይቀናጃሉ።

School’s Out Washington መሪ አራሚዎችን የእርማት ቡድኖችን እንዲያቀናጁ መርዳትን ጨምሮ ሌሎች የእርማቱን ሂደቶች ይመራል። አንዴ የእርማት ቡድኖች ሙሉ በሙሉ የማረሙን እና ውጤት የመስጠቱን ሂደት ሲጨርሱ SOWA ከሁሉም ቡድኖች የመጡትን ውጤቶች ይመለከታል።

# የፕሮፖዛል እርማት መስፈርቶች

ሶስት የትኩረት አካባቢዎች ለመጠይቁ እርማት ወጥ ቀርጽ ይሰጡታል። የውጤት መስጫ ሳጥኑን በመጠቀም አራሚዎች እንዴት እና እስከምን ድረስ የሚለውን ይቃኛሉ

| | |
|---|---|
| 1. ፕሮግራሙ ከትምህርት ፍትሀዊነት እጅግ የራቁ ታዳጊዎችን ያገናኛል። | ከአጠቃላይ ውጤት 35% |
| 2. በሚከተሉት ቡድኖች ውስጥ ያሉት ግለሰቦች ቅድሚያ የሚገለገለውን ህዝብ የሚያንጸባርቁ ናቸው፡ 1) የፕሮግራሙ ሰራተኛ እንዲሁም/አልያም ከታዳጊዎች ጋር | ከአጠቃላይ ውጤት 20% |

| | |
|---|---|
| በቀጥታ የሚሰሩ በጎ ፈቃደኞች፣ 2) የፕሮግራሙ አመራር፣ 3) በጎ ፈቃደኛ የቦርድ አባላት | |
| 3. ፕሮግራሙ ማህበራዊ ግንኙነቶችን፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲሁም ከቤት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎችን ለታዳጊዎች ይገልጻል እንዲሁም ይደግፋል በተጨማሪም የፕሮግራሙ ትግበራ እቅድ እነዚህ የፕሮግራሙ ቅድመ ሁኔታዎች እንደሚሟሉ እና ለተገልጋዮች ታዳጊዎች መሰረታዊ ፍላጎቶች እንዲሁም መስህቦች ምላሽ እንደሚሰጡ ያረጋግጣል። | ከአጠቃላይ ውጤት 45% |

ከአራሚዎች ውጤቶች ጋር በአንድነት፣ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ህዝቦች ዘንድ ፍትሀዊ የሆነ ውክልና በግዛቱ ዙሪያ፣ ፍትሀዊ መልከዓምድራዊ ክፍፍል፣ የተሳታፊ ታዳጊዎች ቁጥር፣ እንዲሁም የግንኙነት ሰዓታት ብዛት ለ SOWA እርማት መስፈርት ይሆናሉ። የእርማቱን መስፈርቶች በሚያሟሉ ተፎካካሪ ማመልከቻዎች ዘንድአነስተኛድርጅቶች ተጨማሪ አስተያየቶችን SOWA ለOSPI በሚሰጠው የመጨረሻ የገንዘብ ድጋፍ ምክረ ሀሳብ ይቀበላሉ።

## መልከዓምድራዊ ክፍፍል

ከታች የተቀመጠው ካርታ በግዛቱ ውስጥ ከWashington Department of Children, Youth and Families (DCYF's) የአስተዳደር ክልሎች ጋር የሚዛመዱ ስድስት ክልሎችን ያሳያል። SOWA የ DCYF ክልሎችን የፕሮፖዛል አራሚ ቡድኖች ሲመድብ በመልከዓምድር ለመከፋፈል እንደ አንድ መንገድ ይጠቀምባቸዋል።

በግዛቱ ዙሪያ ለሚደረጉ የገንዘብ ድጋፎች የተቀመጡ ዓላማዎች ለእነዚህ ክልሎች በተወሰኑ በሁለት ቁልፍ የመረጃ ነጥቦች ላይ ይመሰረታሉ፡ ታዳጊዎች 18 እና ከዛ በታች ሆነው በድህነት የሚኖሩ፤ እንዲሁም BIPOC ታዳጊዎች, 18 እና ከዛ በታች። (መረጃዎቹ የተሰበሰቡት ከአሜሪካን ኮምዩኒቲ ሰርቬይ፣2019 ነው።)

ከስር ባለው ካርታ የመቶኛ አቀማመጥ የተመሰረተው በዋሽንግተን ወጣቶች 18 እና ከዛ በታች ሆነው በድህነት የሚኖሩ መቶኛ እና የዋሽንግቶን BIPOC ወጣቶች 18 እና ከዛ በታች በእያንዳንዱ ክልል የሚኖሩ መቶኛዎች መሰረት ነው። በክልል የበጀት ስርጭት አላማዎችን ለመወሰን ወሂቡ እኩል ክብደት ነው የተሰጠው። እነዚህ የጂኦግራፊያዊ ስርጭት አላማዎች ሆነው ሳለ እነሱን ማሳካት ለእያንዳንዱ ክልል በሚገቡ በተለያዩ ብቃት ባላቸው እና ከፍተኛ ደረጃ በተሰጣቸው ፕሮፖዛሎች ተጠባባቂ ይሆናል።



Youth under 18 in Poverty per region (2019) and % BIPOC youth under 18 per region (2019)

## የ ንዘብ ድጋፍ

በክልሉ በሁሉም ቦታዎች ባሉ የ2022 የበጋ መርሃ-ግብሮች የገንዘብ ድጋፍ ይኖራቸዋል። የ2022 የበጋ መርሃ-ግብር የገንዘብ እርዳታ ከ$10,000 እስከ $50,000 ክልል ውስጥ የሚሆን ይሆናል። አመልካቾች በዚህ ክልል ውስጥ የገንዘብ እርዳታ መጠን እንዲጠይቁ ይጠየቃሉ ነገር ግን የሚቀበሉት የገንዘብ መጠን ከተጠየቀው በታች ሊሆን ይችላል።

የተሳካላቸው አመልካቾች የሚከተለውን እንዲያደርጉ ይገደዳሉ፡

- ከSchool’s Out Washington ጋር ኮንትራት ይፈርማሉ። ሀ ናሙና ውልለመረጃ ምክንያቶች ብቻ እዚህ ጋር ተካቷል። የመጨረሻ ውሎች ከናሙና ውሉ መጠነኛ ልዩነቶች ሊኖርት እንደሚችል እባኮን ይገንዘቡ። ጉዳዩ ይህ ከሆነ የውል ፊርማ ሳይጠየቅ በፊት ለተመረጡ አመልካቾች ለውጦች የሚደምቁ ይሆናል።
- በቂ የተጠያቂነት መድን ማስረጃ ያቀርባሉ።[4] የመድን መስፈርቶች ዝርዝር በናሙና ውል ውስጥ ተካተዋል
- የገንዘብ እርዳታ ማስተላለፍን ለማመቻቸት ቅፆችን ሞልተው ይርሳሉ
- የተሟሉ የድርጅት መገለጫዎችን በ Elevate Washington
- ማመልከቻቸውን ካስገቡ በኋላ በ2022 የበጋ መርሃ-ግብራቸው ላይ ምንም አይነት ለውጦች ካሉ ያንን በአጭሩ ለውጦችን የሚዘረዝር ቅፅ ይሞላሉ።
- የመጨረሻ የትረካ ሪፖርት ያስገባሉ

---

[4] በ2022 የበጋ መርሃ-ግብር የገንዘብ እርዳታ በኩል የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው ድርጅቶች SOWA ከOSPI ባለው ውል ውስጥ እንደ የSOWA ንዑስ ተቋራጮች ተብለው ይቆጠራሉ። በመሆኑም፣ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ድርጅቶች የውል ገደቦችን የሚያሟላ የተጠያቂነት መድን፣ የሰራተኞች ካሳ መድን እና የመኪና መድን (እንደተገቢነቱ) ጨምሮ የOSPI መስፈርቶችን የሚያሟሉ መድኖችን መያዝ አለባቸው። ገንዘቡ ከመከፈሉ በፊት SOWA እና OSPI እንደ ተጨማሪ መድን አቅራቢ የሚሰይሙ የመድን ሰርተፊኬቶችን SOWA ይፈልጋል።

## የጊዜ ሂደት

| | |
|---|---|
| ኖቬምበር 4, 2021 | RFP ተለቋል |
| ኖቬምበር 10 እና ኖቨምበር 16, 2021 | RFP የመረጃ ክፍለ ጊዜዎች። እዚህ ጋር ይመዝገቡ፡<br>ኖቬምበር 10፣2021፣ 1:00 ፒኤም-2:30ፒኤም<br>ኖቬምበር 16፣2021፣ 9:00ኤኤም-10:30ኤኤም |
| ኖቬምበር 5 - ዲሴምበር 3, 2021 | ቴክኒካል እርዳታ ይኖራል። በTA ላይ ተጨማሪ መረጃ 2022 የበጋ መርሃግብር የገንዘብ እርዳታ ድህረ ገፅ ላይ ይገኛል። |
| ኖቬምበር 9, ኖቬምበር 15, ኖቬምበር 22, እና ኖቬምበር 30, 2021. | FAQዎች በ2022 የበጋ መርሃግብር የገንዘብ እርዳታ ድህረ ገፅ ላይ ዘምነዋል እና ቀርበዋል። FAQ ለማስገባት የመጨረሻ ቀን ኖቬምበር 29, 2021 ላይ ነው። |
| ዲሴምበር 6, 2021 | ማመልከቻዎች የሚያበቁት በ 11:59 PM ነው። |
| ዲሴምበር 9, 2021 - ጃንዋሪ 2022 መጨረሻ አከባቢ | ማመልከቻዎች በSOWA ቡድን እና አቻ ገምጋሚዎች ይገመገማል |
| በፌብሯሪ 2022 አጋማሽ | OSPI ግምገማ እና የገንዘብ እርዳታ ምክሮች ፍቃድ መስጠት።<br><br>ለተሳካላቸው አመልካቾች የገንዘብ እርዳታ ማሳወቅ። |
| ማርች 15 2022 | የተሳካላቸው አመልካቾችማመልከቻቸውን ካስገቡ በኋላ በ2022 የበጋ መርሃ-ግብራቸው ላይ ምንም አይነት ለውጦች ካሉ ያንን በአጭሩ ለውጦችን የሚዘረዝር ቅፅ ይሞላሉ። |
| ማርች አጋማሽ | 2022 የበጋ መርሃ-ግብር ሲምፖዚየም |
| በሜይ 13, 2022 | የገንዘብ እርዳታ ክፍያ |
| ጁን 2022 - ሰፕቴምበር 2022 | የበጋ መርሃ-ግብር ትግበራ |
| ሴፕቴምበር 30, 2022 | የመጨረሻ ሪፖርት መድረስ አለበት። |

## የማመልከቻ ጠቅላላ እይታ

የ2022 የበጋ መርሃ-ግብር የገንዘብ እርዳታ ማመልከቻ ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጉ መረጃ እና ጥያቄዎች ከስር ተዘርዝረዋል። ተቆልቋዮች እና የትረካ ምላሾችን ያካትታሉ።

የማመልከቻው አብነት በመስመር ላይ ያለው ማመልከቻ መጀመርያ ላይ ቀርቧል። አመልካቾች ጥያቄዎችን ለመገምገም እና መልስ ለመጻፍ አብነቱን እንዲጠቀሙ እንመክራለን። አብነቱ ላይ አንዴ ምላሾች እንዳለቁ አመልካቾች የመስመር ላይ ማመልከቻ ቅፁ ላይ ለማስገባት መገልበጥ ይችላሉ።

ማመልከቻዎች የሚገቡት [በመስመር ላይ መሆን አለበት።](#) አመልካቾች ስራቸውን አድነው ወደ ማመልከቻቸው መመለስ ይችላሉ። በማመልከቻው ውስጥ እንዴት ወደ ማመልከቻቸው አድነው መመለስ እንደሚችሉ የሚያሳዩ መመሪያዎች አሉ። ማመልከቻዎች መጠናቀቅ እናበሰኞ ዲሴምበር 6, 2021 በ 11:59 PM መግባት አለባቸው።

## የብቃት መረጃ

እባኮን ድርጅቶ ለገንዘብ እርዳታ ለማመልከት ብቁ መሆኑን ያረጋግጡ፡

- ድርጅቶ፡
  - ለወጣቶች በ 2022 የበጋ መርሃ-ግብር ያዘጋጃል።
  - የWashington State Department of Health ፕሮቶኮሎችን ይከተላል
  - ለትርፍ ያልተቋቋመ ማህበራዊ መሰረት ያለው ድርጅ፣ አነስተኛ ንግድ ወይም የህዝብ ኤጀንሲ ነው።
  - በዋሽንግተን ክልል በK-12 ትምህርት ቤት የተመዘገቡ ወይም የሚቀርቡ አገልግሎቶችን የሚጠቀሙ ከ4-21 ያሉ ወጣቶችን ያገልግላል።

- የድርጅቶ የ2022 የበጋ መርሃ-ግብር፡
  - በወጣቶች መሃል ያሉትን የማህበራዊ ግንኙነቶች ለማጠናከር የተቀረፁ እንቅስቃሴዎችን ያካትታል
  - አካላዊ እንቅስቃሴዎችን ያካትታል
  - የውጪ እንቅስቃሴዎችን ያካትታል
  - በብዙ ቀናት እና/ወይም በብዙ ሳምንታት የሚቀርብ ይሆናል
  - በአካል ወይም በአብዛኛው በአካል የሚቀርብ ይሆናል

ፓርኮች የስራ መስኮች እና የትምህርት ቤት ወረዳዎች ብቁ አይደሉም። የገንዘብ ምንጮች ለ 1:1 የመርሃ-ግብር አሰራር ወይም ለሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ሊውል አይገባም።

## መርሃ-ግብር/ድርጅት መረጃ፡

- የበጋ መርሃ-ግብር በገንዘብ የሚረዳው በትርፍ ባልተቋቋመ ድርጅት ነው፡
  - አዎ
  - አይ

  *አዎ ከሆነ፣ ከእርዳታ ሰጪው ድርጅት የገንዘብ እርዳታ ግንኙነት የሚያረጋግጥ የተፈረመበት ደብዳቤ እንዲሰቅሉ ይገደዳሉ።

- በ2022ቱ የበጋ መርሃ-ግብር ተገልግለው የዚህ ማመልከቻ ትኩረት የሆኑ ሃገራትን ይምረጡ:

- የድርጅቱ ህጋዊ ስም፡

- የገንዘብ እርዳታ የሚያቀርብ ድርጅት ስም፣ የሚቻል ከሆነ፡

- የስራተኛ መለያ ቁጥር (EIN Employer Identification Number)፡
  *ያስተውሉ*: መርሃ-ግብሩ/ድርጅቱ የገንዘብ እርዳታ አቅራቢ ካለው፣ እባኮትን የገንዘብ እርዳታ አቅራቢዎን EIN ያስገቡ

- የተዋሀደ የንግድ መለያ (UBI Unified Business Identifier) ቁጥር፡
  *ያስተውሉ* መርሃ-ግብሩ/ድርጅቱ የገንዘብ እርዳታ አቅራቢ ካለው፣ እባኮትን የገንዘብ እርዳታ አቅራቢዎን UBI ያስገቡ።

- የድርጅቶ በቅርብ በትጠናቀቀው የበጀት አመት አጠቃላይ የስራ ወጪዎች ምን ያህል ነበሩ?

- የበጀት አመቱ ያለቀው መቼ ነው?

- የድርጅት አይነት፡
  *ያስተውሉ፡* መርሃ-ግብሩ/ድርጅቱ የገንዘብ እርዳታ ሰጪ ካለው እባኮትን የገንዘብ እርዳታ ሰጪ ድርጅቱንን አይነት ያስገቡ
  - ለትርፍ ያክልተቋቋመ
  - አነስተኛ ንግድ
  - የህዝብ ኤጀንሲ (እባኮን ይለዩ)፡ ______
  - ሌላ (እባኮን ይለዩ)፡ ______

- የመጀመርያ የስራ አድራሻ
  - ሙሉ አድራሻ (ከተቻለ አፓርታማ/ክፍል/የሚተገበር ከሆነ ቢሮ ያካተተ)
  - ከተማ/ከተማ
  - ክልል
  - ዚፕ ኮድ
  - ካውንቲ

- ማብራሪያ: Pየድርጅቶን አጠር ያለ ማብራሪያ ያቅርቡ (ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ አገልግሎቶች፣ ትኩረት) ከፍተኛ የቃላት ብዛት 200 ነው።
  *ያስተውሉ* ይህ መረጃ በኤሊቬት ዋሽንግተን ይካተታል።

- የቦታ ስም፡
  *ያስተውሉ:* በብዙ ቦታዎች ቦታ ሆነው እያመለከቱ ከሆኑ እባኮን እዚህ ካሉት የአንዱን ቦታ ስም እና አድራሻ ብቻ ያካቱ።

- የቦታ ስም
  *ያስተውሉ* የቦታው መገኛ ዋሽንግተን ውስጥ መሆን አለበት
  - ሙሉ አድራሻ (ከተቻለ አፓርታማ/ክፍል/ቢሮ ያካተተ)
  - ከተማ/ከተማ
  - ክልል(WA)
  - ዚፕ ኮድ
  - ካውንቲ

- 2022 የበጋ መርሃ-ግብር ስም፡

- ማብራሪያ: የዚህን መርሃ-ግብር አጠር ያለ ማብራሪያ ያቅርቡ(ለማን እንደሆነ፣ የመርሃ-ግብር ትኩረት) ከፍተኛ የቃላት ብዛት 150 ነው.

*ያስተውሉ* ይህ መረጃ በኤሊቬት ዋሽንግተን ይካተታል።

- የአመልካች ድርጅት፣ እና በታዎች እና መርሃ-ግብር ስሞች እና አድራሻዎች እዚህ ሪፖርት እንደተደረጉ በኤሊቬት ዋሽንግተን የህዝብ የወጣቶች መርሃ-ግብር ማውጫ ውስጥ ይካተታሉ። የበታው አድራሻ ሚስጥራዊ ከሆነ በመርሃ-ግብሩ ማውጫ ላይ እንዳይታይ እዚህ ጋር ጥያቄ ያስገቡ።
    - አድራሻ ሚስጥራዊ አይደለም - አዎ ማውጫው ላይ ለማስቀመጥ
    - አድራሻ ሚስጥራዊ ነው - በማውጫው ላይ አያስቀምጡ

**የፕሮፖዛል ጥያቄዎች፡**

**የትኩረት አከባቢ #1፡ መርሃ-ግብሩ ወጣቶችን ከትምህርት ፍትህ በጣም አርቆ ያሳትፋል። ይህ የትኩረት አከባቢ የውጤቱን 35% ይይዛል።**

ከስር ላሉት ጥያቄዎች የሚሰጡት መልሶች የገንዘብ እርዳታ እየፈለጉለት ላሉት ለ2022ቱ የበጋ መርሃ-ግብር የተለዩ መሆን አለባቸው።

a. ከታች ያለው ጥያቄ (1b) በበጋው መርሃ-ግብር በእያንዳንዱ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምድቦች ውስጥ በመቶኛ ምን ያህል ወጣቶች እንዳሉ እንዲነግሩን ይጠይቃል። ስለወጣቶቹ መረጃ ከማቅረቦ በፊት የመረጃ ምንጭን እባኮን ይንገሩን፡
    - መቶኛዎቹ በወጣት ወይም ቤተሰብ ሪፖርት በተደረገ መረጃ መሰረት ናቸው።
    - መቶኛዎቹ በተቀራራቢ የመረጃ ምንጭ እንደ የትምህርድ ቤት ወረዳ ወይም የህዝብ ቆጠራ መረጃ መሰረት ናቸው።
    - መቶኛዎቹ ስለ ወጣቶች ማህበረሰባችን ባለን እውቀት የተሰሩ ግምቶች መሰረት ናቸው።
    - በአሁን ሰዓት ለዚህ ማንኛውም መረጃ ተተኪ ወሂብ አንሰበስብም ወይም የለንም እና ለዚህ ጥያቄ በመቶኛ ለመገመት አልተመቸንም።

    **በቅድሚያ በሚሰጣቸው የህዝብ ብዛቶች ላይ መቶኛዎችን የሚያቀርቡ ካላቀረቡ እንኳን ሁሉም አመልካቾች ስለ ወጣት ማህበራቸው ዘርዘር ያለማብራሪያ ከታች በጥያቄ 1ሠ ማቅረብ አለባቸው።**

b. አባኮን በእነዚህ ምድቦች ስር ያሉ በ2022 የበጋ መርሃ-ግብሮ የሚሳተፉ ወጣቶች መቶኛዎች ይገምቱ። ብዙ ወጣቶች በተለያዩ መደቦች ስር ሊወድቁ እንደሚችሉ እንረዳለን፤ መቶኛዎቹ ተደማምረው 100% መሆን አይጠበቅባቸውም። እባኮን ይህንን ባለፈ የመርሃ-ግብር ወሂብ፣ የጊዜው የምዝገባ ወሂብ፣ ወይም ሌላ እንደ የትምህርት ቤት የስነ ህዝብ አወቃቀር ወሂብ ተቀራራቢ የወሂብ ምንጭ ላይ ይመስርቱ። ስለ ምህበርሰቦ በሚቀጥለው ትረካ እንዲነግሩን እድል ይኖሮታል፡

    በ2022 የበጋ መርሃ-ግብሮ ላይ ከውስን ቅድሚያ ከሚሰጣቸው የህዝብ ብዛት ወጣቶች ይሳተፋሉ ብለው ካልጠበቁ እባኮን ዜሮዎችን ያስፍሩ። ለዛ ቅድሚያ የሚሰጠው የህዝብ ብዛት ግምቶች የቀረቡ ካልሆነ እባኮን ባዶ ይተውት። “ባሁኑ ጊዜ ይህንን ወሂብ አንሰበስብም” ተመርጦ ካልሆነ በቀር ለዚህ ጥያቄ ወሂብ ገባር ማድረግ አለበት፡

    - በድህነት ውስጥ ያሉ ወጣቶች፣ ለነጻ ወይም ቅናሽ ዋጋ ላለው ምሳ ብቃት መሰረት ሲለካ: __%
    - BIPOC ወጣቶች: __%
    - ስደተኛ ወጣቶች: __%

- ስደተኛ እና/ወይም ስደተኛ ወጣቶች፡ __%
- የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች፡ __%
- የጎዳና ተዳዳሪነትን እያሳለፉ ያሉ ወጣቶች፡ __%
- በአሳዳጊ እንክብካቤ ስር ያሉ ወጣቶች፡ __%
- LGBTQ ወጣቶች፡ __%
- በወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ የሚሳተፉ ወጣቶች፡ __%
- አካላዊ፣ እድገታዊ እና/ወይም የአይምሮ እክሎችን ጨምሮ እክሎች ያላቸው ወይም ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎት ያላቸው ወጣቶች፡ __%

c. አንድ ወይም ከዛ በላይ ቅድሚያ የሚሰጣቸው የህዝብ ብዛት ወካዮች የሆኑ የመርሃ-ግብሮ ወጣቶች አጠቃላይ መቶኛ እባኮትን ይገምቱ፡፡፡ __%

d. መርሃ-ግብሮ BIPOC ወጣቶችን የሚያገለግል ከሆነ እባኮትን መቶኛዎች የእያንዳንዳቸው የእነዚህ የBIPOC የወጣት ህዝብ ተወካይ የሆኑ ወጣቶች ያቅርቡ። ብዙ ወጣቶች በተለያዩ መደቦች ስር ሊወድቁ እንደሚችሉ እንረዳለን፤ መቶኛዎቹ ተደማምረው 100% መሆን አይጠበቅባቸውም።
    - አሜሪካዊ ህንዳዊ/የአላስካ ተወላጅ: __%
    - ኤሲያዊ/ኤሲያዊ-አሜሪካዊ: __%
    - ጥቁር/አፍሪካዊ-አሜሪካዊ: __%
    - ሂስፓኒክ ወይም ላቲኖ/a/x ትውልድ: __%
    - መካከለኛ ምስራቅያዊ ወይም ሰሜን አፍሪካዊ: __%
    - ዘረ-ብዙ: __%
    - የሃዋዪ ተወላጅ/የፓሲፊክ ደሴት ነዋሪ: __%

e. **ትረካ:** አንድ ወይም ከዛ በላይ ቅድሚያ የሚሰጣቸው የህዝብ ብዛት ወካዮች እንዴት እንደሚሆኑ ጨምሮ በ2022 የበጋ መርሃ-ግብሮ ወጣቶች እንዴት እንደሚሳተፉ ንገሩን። መርሃ-ግብሮ እንዴት ከቅድሚያ የሚሰጣቸው የህዝብ ብዛት ቡድኖች የሆኑ ወጣቶችን እንደሚያሳትግ ያብራሩልን።

   **ከፍተኛ የቃላት ብዛት 400 ነው።**

**የትኩረት አከባቢ#2 መርሃ-ግብሩ ከላይ ባለው በጥያቄ #1 እንደተዘረዘሩት ቅድሚያ የሚሰጣቸው የህዝብ ብዛቶችን የሚያንፀባርቅ ባልደረቦች፣ በጎ አድራጊዎች፣ አመራር እና የቦርድ አባላት። ይህ የትኩረት አከባቢ ከውጤቱ 20% ይይዛል።**

a. ማንነታቸው/የኖሩበት ገጠመኞች በየትኛውም የቅድሚያ የሚሰጣቸው የህዝብ ብዛት መደቦች ስር የሚወድቁ ሰዎች መቶኛ እባኮትን ይገምቱ።
    - በ2022 የበጋ መርሃ-ግብር በቀጥታ ከወታቶች ጋር የሚሰሩ ባልደረቦች እና በጎ አድራጊዎች: __%
    - የ2022 የበጋ መርሃ-ግብሩን የሚያዩ እና የሚቆጣጠሩ የመርሃ-ግብሩ መሪዎች: __%
    - የመርሃ-ግብሩ/የድርጅቱ የቦርድ አባላት: __%

b. **ትረካ:** የመርሃ-ግብሮ ባልደረቦች፣ በጎ አድራጊዎች፣ አመራር እና የቦርድ አባላት እንዴት ቅድሚያ የሚሰጣቸው የህዝብ ብዛቶችን እንደሚያንፀባርቁ (የሚጋሩ ማንነቶች ወይም ተመሳሳይ የኖሩባቸው ገጠመኞች) ያብራሩ።

   **ከፍተኛ የቃላት ብዛት 350 ነው።**

**የትኩረት አከባቢ#3: ፕሮግራሙ ማህበራዊ ግንኙነቶችን፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲሁም ከቤት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎችን ለታዳጊዎች ይገልጻል እንዲሁም ይደግፋል በተጨማሪም የፕሮግራሙ ትግበራ እቅድ እነዚህ የፕሮግራሙ ቅድመ ሁኔታዎች እንደሚሟሉ እና ለተገልጋዮች ታዳጊዎች መሰረታዊ ፍላጎቶች እንዲሁም መስህቦች ምላሽ እንደሚሰጡ ያረጋግጣል። ይህ የትኩረት አከባቢ ከውጤቱ 45% ይይዛል።**

የመርሃ-ግብር አይነት፡ በ2022 የበጋ መርሃ-ግብር የገንዘብ እርዳታ ምን አይነት የመርሃ-ግብር አያያዝ እንደሚያቀርቡ እባኮን ይንገሩን፡ (የሚሆኑትን ሁሉ ምልክት ያድርጉባቸው)

- አካዳሚክ
- ስዕል እና ባህል
- የሙያ አሰሳ እና የስራ ስልጠና
- የልጅ እንክብካቤ
- መሪነት፣ አገልግሎት እና ማህበራዊ ፍትህ
- አካላዊ እንቅስቃሴዎች እና ስፖርቶች
- ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና እና ሂሳብ (STEM Science, Technology, Engineering and Math)
- አገልግሎት እና እርዳታ
- ሌላ (እባኮን ግልፅ ያድርጉ): ________

የ2022 የበጋ መርሃ-ግብር የሚያገለግላቸው ወጣቶች፡ (የሚሆኑትን ሁሉ ምልክት ያድርጉባቸው)

- 4-12
- 13-18
- 19-21

የሚገለገሉ የወጣቶች ቁጥር፡

- <20 ወጣቶች
- 20-50 ወጣቶች
- 51-100 ወጣቶች
- > 100 ወጣቶች

መርሃ-ግብሩ የሚቀርበው፡

- በአካል ብቻ
- ድብልቅ፡ በአካል እና ምናባዊ

የማስገባት አይነት መርሃ-ግብር?

- አዎ
- አይ

የመርሃ-ግብር ቆይታ

- 1-2 ሳምንታት
- 3-5 ሳምንታት
- 6 ወይም ከዛ በላይ ሳምንታት

መርሃ-ግብሮ በሳምንት ስንት ቀናት ነው የሚሰጠው?

- 1-2 ቀናት በሳምንት
- 3-4 ቀናት በሳምንት
- 5 ቀናት በሳምንት
- ሌላ (እባኮን ግልፅ ያድርጉ)፡ ________

የመርሃ-ግብር የቀን እርዝማኔ፡

- 1-2 ሰዓታት በቀን
- 3-4 ሰዓታት በቀን
- 5-6 ሰዓታት በቀን
- 7-8 ሰዓታት በቀን
- ከ8 ሰዓታት በቀን በላይ

**ትረካ:** የበጋ መርሃ-ግብሮ የንድፍ እና የትግበራ እቅድ ያብራሩ። ***ምን*** እንደሚሰሩ ***ለምን*** ንድፎ ለሚያገለግሏቸው ወጣቶች መልስ ሰቺ እንደ ሆነ እና ***እንዴት*** መርሃ-ግብሮን እንደሚተገብሩ ያስቡ። እነዚህን በሙሉ በመልሶ ያካቱ።

1. የ2022 የበጋ መርሃገ-ግብሮ አጠቃላይ እይታ ያቅርቡ። እንዴት አድርገው ሊተገብሩት ነው ያቀዱት? *(በዚህ ግዜ በተለያዩ ምክንያቶች የትግበራው ብዙ ገፅታዎች ግልጽ ላይሆኑ እንደሚችሉ ገምጋሚዎች ይረዳሉ ነገር ግን እቅዶ ለምን የሚቻል እንደሆነ እንደሚያምኑ እና መርሃ-ግብሩን እንዴት በስኬት ሊያስነሱ እንዳሰቡ ኣባኮን ባጭሩ ይግለጹ።)*

**ከፍተኛ የቃላት ብዛት 200 ነው።**

2. የማህበራዊ ግንኑነቶችን ለማጠናከር የሚያቀርቧቸውን እንቅስቃሴዎች በዝርዝር ያብራሩ። *(ምሳሌዎች ያቅርቡ። አቀራረቡ በእድሜ ምድብ ይለያያል? መርሃ-ግብሮ እንዴ በወጣቶች መሃል የማህበራዊ ግንኑነቶችን እንደሚያጠናክር ገምጋሚዎች እንዲረዱ ያግዟቸው)*

**ከፍተኛ የቃላት ብዛት 200 ነው።**

3. መርሃ-ግብሩ ምን አይነት አካላዊ እንቅስቃሴዎችን ያካትታል? *(ግልጽ ይሁኑ። እንቅስቃሴዎች በእድሜ ምድብ ይለያያሉ? ለወጣቶች የሚቀርበው በትክክል ምን እንደሆነ ለገምጋሚዎች ያስረዱ።)*

**ከፍተኛ የቃላት ብዛት 150 ነው።**

4. መርሃ-ግብሩ ምን አይነት የውጪ እንቅስቃሴዎችን ያካትታል? *(ግልጽ ይሁኑ። እንቅስቃሴዎች በእድሜ ምድብ ይለያያሉ? ለወጣቶች የሚቀርበው በትክክል ምን እንደሆነ ለገምጋሚዎች ያስረዱ።)*

**ከፍተኛ የቃላት ብዛት 150 ነው።**

5. ለቅድሚያ ለሚሰጠው የህዝብ ብዛት ፍላጎት ለምን የመርሃ-ግብሮ ሞዴል ውጤታማ እና መልስ ሰጪ እንደ ሆነ ያብራሩ። *(ከመርሃ-ግብሮ ቅርጽ በስተጀርባ ያለውን አስተሳሰብ ገምጋሚዎች እንዲረዱ ያግዙ።)*

**ከፍተኛ የቃላት ቁጥር 250 ነው።**

**የገንዘብ እርዳታ ጥያቄ**: 2022 የበጋ መርሃ-ግብሮች በ$10,000 እና $50,000 መሃል ሊጠይቁ ይችላሉ። የገንዘብ እርዳታዎች በሴፕቴምበር 30, 2022 ማለቅ አለባቸው።

በ10,000 እና 50,000 መሃል ያለ ቁጥር ማስገባት አለቦት

**የምስክር ወረቀቶች፡**

ይህንን ቅፅ እየሞላ ያለው ሰው ስም፡

የኢ-ሜይል አድራሻ፡ የስልክ ቁጥር፡

የገንዘብ እርዳታ የሚያገኙ አመልካቾች በሙሉ የተፈረመበት የተጠናቀቀ W-9 እንዲያስገቡ ይገደዳሉ። የገንዘብ እርዳታ በኤሌክትሮኒክ መንገድ በአውቶሜትድ ማጽጃ ቤት (ACH Automated Clearing House) በኩል ይከፈላሉ። School's Out Washington በዶክዩሳይን የACH ፍቃድ መስጫ ቅፅ እና W-9 ቅፅ ለስኬታማ አመልካቾች ይልካል። የእነዚህ ዶክዩመንቶች መመላስ በሪሲቱ ሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሆን ይገደዳል። የACH ቅፅ እና W-9 ጥያቄ ለማን መላክ እንዳለበት እባኮን ግልጽ ያድርጉ.

ስም፡ ኢ-ሜይል አድራሻ፡

የገንዘብ እርዳታ የሚያገኙ አመልካቾች በሙሉ ከSchool’s Out Washington ጋር ውል መፈራረም ይጠበቅባቸዋል። ውሉ ለፊርማ ማን ጋር መላክ እንዳለበት እባኮን ግልጽ ያድርጉ።

ስም፡ ኢ-ሜይል አድራሻ፡

የገንዘብ እርዳታ ካገኘ በዚህ ማመልከቻ ውስጥ ያለውን የገንዘብ ነክ መረጃ ለማረጋገጥ አመልካቹ School’s Out Washington የገንዘብ እርዳታ ቀኑን ቀጥሎ ለሚቀጥሉት ስድስት አመታት በሁሉም ተገቢ ጊዜያት የ990 ቅፁን እና ሌሎች ገንዘብ ነክ መረጃዎችን ማግኘት እንዲችል ፍቃድ ይሰጣል።

እባኮን ሁሉንም ሳጥኖች ምልክት ያድርጉባቸው። (የአነስተኛ ንግድ ማብራርያ ደግመው ማየት ከፈለጉ ይህንን ማስፈንጠሪያ ይምረጡ RCW19.85.020)

“በአመልካቹ ድርጅት ቦታ ሆኜ ይህንን ማመልከቻ ለማስገባት ፍቃድ ማግኘቴን አረጋግጣለሁ።”

“"ይህን ማመልከቻ በመፈረም አመልካች ድርጅቱም ሆነ ርእሰመምህራኖቹ በአሁኑ ጊዜ እገዳ የተጣለባቸው፣ የታገዱ፣ የመታገድ ጥያቄ የቀረበባቸው፣ ብቁ አይደሉም የተባሉ ወይም በማንኛውም የፌደራል ወይም የክልል ክፍል ወይም ኤጀንሲ በዚህ ግብይት እንዳይሳተፉ በፈቃደኝነት የተገለሉ አለመሆናቸውን አረጋግጣለሁ።"

“ሳመለክት እንደ አነስተኛ ንግድ ካመለከትኩ፣ የእኔ ንግድ በRCW19.85.020 የቀረበውን የአነስተኛ ንግድ ትርጉም እንደሚያሟላ አረጋግጣለሁ።”

“የተገለፀው መርሃ-ግብር ሃይማኖታዊ አምልኮን፣ የአካላዊ እንቅስቃሴን ወይም መመሪያን እንደማይጨምር አረጋግጣለሁ።” ማመልከቻው ከተሳካ ማንኛውም ተሳታፊዎች መገልገያዎችን ለማግኘት በማንኛውም ሀይማኖታዊ አምልኮ፣ አካላዊ እንቅስቃሴ ወይም መመሪያ ላይ መሳተፍ አይጠበቅባቸውም።

"በዚህ ማመልከቻ ውስጥ የቀረበው መረጃ እና በማንኛውም ደጋፊ ሰነዶች እና ቅጾች ውስጥ የቀረበው መረጃ በሁሉም ነገራዊ ጉዳዮች እውነት እና ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ። እንዲሁም በዚህ ማመልከቻ ላይ ያሉ ማንኛውም የውሸት መግለጫዎች ወይም ሆን ተብሎ የቀሩ እውነታዎች የገንዘብ እርዳታውን እንድመልስ ወይም ሌሎች ለበተሳሳተ መረጃ የማጭበርበር ህጋዊ እርምጃዎችን ተገዢ ሊያደርገኝ እንደሚችል ተረድቻለሁ።”